# ETNK WEEKLY NEWS 09-12-2017

የአማራና የኦሮሞ የፖለቲካ ሀይሎች አንድ የጋራ የትብብር መድረክ በመፍጠር ህወሓትን ማስወገድ ይገባቸዋል ተባለ

የመቀሌው ስብሰባ በሹም ሽር መግለጫ ጋጋታ የታጀበ የጥልቅ ተሃድሶው ውጤት ከግር ጥፍሩ እስከ ዶቃ ማሰሪያው በንጹሀን ደም ለጨቀየው የሌባና የሰው በላ የወያኔ ቡድን ለዳግም ግፍ ለበለጠ አፈና በሚያመቸው መልኩ የጭካኔ ጠበብቶቹን መሪ አድርጎ ሊዘምትብን መዘጋጀቱን ገልጿል። የህወሃት ትዕቢት ጨለምተኝነቱና ለህዝብ ያለው ንቀት ድንበር የለሽ በመሆኑ አማራና ኦሮሞን በእሳትና ጭድ መስሎ በአደባባይ የተናገረውን ስቅላት ይገባው የነበረን ጸረ ሕዝብ ግለሰብ ከፍ ላለ ወንበር መሾሙ ከፍ ላለ ጥፋት መዘጋጀቱን የሚያስይ ነው።አማራና ኦሮሞ እንደ ድርና ማግ የተጋመዱ፣ እንደ ሥርገኛ ጤፍ የተቀላቀሉ ዘመን ተሻጋሪ ዕድል ፈንታና ጽዋ ተርታቸው አንድ የሆነ ወንድማማች ነገዶች ናቸው።ከዚህ አንጻር ማንም ምንም ይበለው ከበስተጀርባው ያነገበው ስውር ተልዕኮ ይኑረው አይኑረው ፖለቲካዊ ፋይዳው፣ ታክቲካዊ አሰላለፉ በፈለገው ደረጃ ይተርጎም የባህር ዳሩ የአማራና የኦሮሞ የፖለቲካና የማህበረሰብ መሪዎች የጋራ ምክክር መድረክ ታሪካዊነቱን ማንም ሊነሳው አይችልም። ይህ ያልተለመደና ያልተጠበቀ የፖለቲካ ቡድኖች ግንኙነት ሊያስገኝ የሚችለው ማህበራዊ፣ ሰብዓዊና፤ አብሮነታዊነትን የሚያጠናክር ተግባር ተምሳሌታዊ ነው። በሳትና ጭድነት ተፈርጀው እርስ በእርሳቸው እንዲጫረሱና እንዲጠፋፉ ዕቅድ የተነደፈላቸው ወገኖች የህወሃትን የአፓርታይድ ከፋፍለህ ግዛው የጥፋት ፖሊሲ ያከሸፋበት አጋጣሚም ነው። የአማራውና ኦሮሞው የዘመናት አብሮነትና ወንድማማችነትን የሚያጠናክር ታሪካዊ ክንውን እና አዲስ ምዕራፍ ከፋችም ሆኗል።ክፉ ወያኔዎች በገነቡት የጥላቻ ግምብ አማራና ኦሮሞን የመለያየት ሴራቸው እስከዘላለም እንዲቀጥል ሰይጣናዊ ዘመቻ ሲያቀናብሩ ኖረዋል። በዚህ ሁሉ ሁኔታ በወያኔ አዝማችነትና ጥላቻን በተጋቱ ስሜታዊ እርምጃ የብዙዎች ንጹሀን አንገት ተቀልቷል።ብዙ ሺዎች ወልደው ከከበዱበት፣ ጥረው ግረው ሀብት ንብረት ካፈሩበት በግፍ ተፈናቅለው ለስደትና እንግልት ተዳርገዋል።ከዚህ አስፈሪ ሐገር አፍራሽና ትውልድ በታኝ የጥፋት አዙሪት ሀገራችንን ለመታደግ የሁለቱ የፖለቲካ ሀይሎችና ሊሂቃን በጋራ ለማሰለፍ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል።ሁለቱ ወገኖች ጊዜውን ያልዋጀ ፉክክርና ገመድ ጉተታ አስፈላጊው የትብብር እንቅስቃሴ እንዳይደረግ እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል።አሁንም አስተማማኝ ለውጥ እንዲመጣ የሚያስችል በየትኛውም የፖለቲካ አሰላለፍ ላይ ያሉ ወገኖች የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ተረድተው፤ አንድ የጋራ የትብብር መድረክ በመፍጠር ህወሓትን ማስወገድ ይገባል ሲል የቀድሞው መዐሕድ አመራር አባል ሐይለገብርኤል አያሌው አርብ እለት ጎልጉል ጋዜጣ ላይ ባወጣው ጹሁፉ ጠይቋል።በሌላ በኩል የፍልስፍና ምሁሩ ዶክተር ዳኛቸው አሰፋ ባለፈው ሳምንት በኦሮሚያ ሚዲያ ኔትዎርክ ቀርቦ የአማራና ኦሮሞ ህዝብ በርካታ ታሪኮችን የተጋራ አንድ ህዝብ ነው ሲሉ ገልጸዋል።ወሳኝ በሆነ ኢትዮጵያ የታሪክ ምዕራፍ ላይ የኦሮሞና አማራ ያልተሳተፈበት የለም።የአኗኗር ዘይቤው፣ ባህሉ፣ወጉና ቋንቋው የተወራረሰ ነው በማለት አስተያየታቸውን አካፍለዋል።

**********

የኢትዮጵያ መንግሥት በተቃዋሚዎችና በጋዜጠኞች ላይ የኮምፒውተር ሥለላ እያደረገ መሆኑ ተገለጸ

የኢትዮጵያ አምባገነን ስርዓት በተቃዋሚዎች ላይ በአዲስ መልኩ የተጠናከረ የኮምፒውተር ሥለላ እያደረገ መሆኑን አለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ተሟጋች የሆነው ሂዩማን ራይትስ ዎች አስታወቀ።መቀመጫውን በካናዳ ያደረገውን ሲቲዚን ላብ የተባለ የምርምር ተቋም የሰረውን ጥናት ጠቅሶ መረጃውን ይፋ ያደረገው ሂዩማን ራይትስ ዎች ጥቃቱ ያነጣጠረው በውጭ ሀገር የሚኖሩ ፖለቲከኞችን፣ጋዜጠኞችንና ምሁራን ላይ መሆሆኑን ገልጿል።የምስራቅ አፍሪካ የሂዩማን ከፍተኛ ሪሰርቸር ፌሊክስ ሆርን ሐሙስ እለት በቲውተር ገጹ ላይ እንደገለጸው የኮምፒውተር መሰለያ ሶፍት ዌር በእስራኤል ከሚገኝ ድርጅት በከፍተኛ ወጭ የተገዛ መሆኑን ጠቅሷል።ሶፍት ዌሩም የተላኩ ኢሜሎችን፣ በስካይፒ የተደረጉ ቃለ ምልልሶችን እንዲሁም በተጠለፈው ኮምፒውተር ዙሪያ የሚደረጉ ማንኛውንም እንቅስቃሴ ማሳየት የሚችል ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት የአገዛዝ ስርዓት ከዚህ ቀድም የሚቃወሙትን ድርጅቶችንና ግለሰቦች ለመሰለል ከፍተኛ የሀገሪቱን መዋለ ንዋይ እንደሚያፈስ ይታወቃል።በተለያየ ጊዜም መቀመጫቸውን በውጭ ያደረጉ የሚዲያ ተቋማት በሀገር ውስጥ እንዳይታዩና እንዳይሰሙ ሚሊዮን ዶላር እየከፈለ ጃም ሲያደርግ መቆየቱ የሚታወስ ነው።

**********

ብአዴን አስቸኳይ ኮንፈረንስ እንዲያደርግ የእነ ስብሀት ነጋ ቡድን ከጀርባ መወሰኑ ታወቀ

የብአዴንና ኦህዴድ ለህዝብ ተቆርቋሪ ካድሬዎች የኢህአዴግ ምክር ቤትና ስራ አስፈጻሚ አወቃቀር እንዲስተካከል መጠየቅ መጀመራቸው የህወሓት የአገዛዝ ቡድንን ማስጨነቁን መረጃዎች ጠቆሙ።ህብር ራዲዮ ምንጮቹን ጠቅሶ እንደዘገበው፤የአማራ

ክልል ርዕሰ መስተዳድር የሆኑትን አቶ ገዱ አዳርጋቸውን የወልቃይት የማንነት ጥያቄ በሚል ጉዳዩን ከሒላ መግፋታቸውንና ህዝባዊ እንቅስቃሴውን በተገቢው መንገድ ለመቆጣጠር ፍላጎት አላሳዩም በማለት መፈረጃቸውን ገልጿል።በመሆኑም በአቶ በረከት ስምዖን ፊት አዋራሪነት ብአዴን ድርጅታዊ ኮንፈረንስ በአስቸኳይ እንዲጠራና አቶ ገዱ ከጸረ-ሰላም ሀይሎች ጋር የተባበረ በማለት ከስልጣን እንዲወርድ ተወስኗል።በምትኩም የአማራን ህዝብ በአደባባይ የሚሳደበውን አቶ አለምነው መኮንን የክልሉ ፕሬዚዳንት ሆነው እንዲሾሙ የህወሓት ጠንካራ ፍላጎት መሆኑ ተገልጿል።ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ህዝባዊ ወገንተኝነት እያሳየ የመጣውን የአቶ ለማ መገርሳም የአመራር ቡድን በኢህዴግ ምክር ቤት ለመምታት የእነ ስብሀት ነጋ ቡድን እቅድ መያዙ ተገልጿል።ኦህዴድም ተመሳሳይ ኮንፈረንስ እንዲጠራና እነ ለማ አንስቶ በአሁኑ ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ኩማ ደሜቅሳን ዋና ተዋናይ ማድረግ ያለመ መሆኑ ተዘግቧል። የህወሓት የጀርባ አጥንት የሆነው የደህንነት መስሪያ ቤት በብአዴንና ኦህዴድ ውስጥ ያሉ ህዝባዊ ወገንተኝነት አሳይተዋል የተባሉ ካድሬዎችን ለማሰር፣ለመግደልና ለመሰወር የመለየት ስራ እየሰራ መሆኑ ሾልከው የወጡ መረጃዎች ጠቁዋል።

*******

በደቡብ ሱዳን ውስጥ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰላም አስከባሪ ቡድን የሚፈጸም የወሲብ ብዝበዛን መታገስ እንደማይገባ አንድ የመንግስታቱ ከፍተኛ ባለስልጣን ገለጹ

በደቡብ ሱዳን የሚገኘው የተባበሩት መንግስታት ሰላም አስከባሪ ቡድን፣የሲቪል ሰራተኞችና በጎ ፈቃደኞች ለአንድ የጋራ አላማ በመተማመን ሊሰሩ እንደሚገባ አንድ የተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ ባለስልጣን ገለጹ።የጉዳተኞች መብት ተሟጋች የሆኑት ወይዘሮ ጄን ኮንኖርስ ባለፈው ሳምንት ደቡብ ሱዳንን በጎበኙበት ወቅት እንደገለጹት በእነዚህ ድርጅቶች መካከል የሚፈጠር አለመተማን ህዝቡ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ላይ ያለውን እምነት የሚሸረሽር ነው ብለዋ።የመንግስታቱ ድርጅት ሰላም አስከባሪ ቡድን በደቡብ ሱዳን ወሲባዊ ትኩሳን ያደርሳል በሚል በተለያዩ ወገኖች የሚቀርብ ክስ መኖሩ የሚታወቅ ሲሆን እሳቸው “በሰላም አስከባሪው የተፈጸመ የወሲብ ጥቃት ስለመኖሩ የሚያሳይ መረጃ አላገኘሁም” ብለዋል።ወይዘሮ ጄን ባለፈው ሳምንት ደቡብ ሱዳንን በጎበኙበት ወቅት ከተጎጅዎች፣ከመንግስትና ከሰላም አስከባሪው ቡድን ጋር በመገናኘት መክረዋል።አካባቢውንም ከእንዲህ አይነት ጥቃት ነጻ ለማድረግ እንደሚሰሩ ቃል ገብተዋል።የጉብኝታቸው አላማም በማንኛውም መንገድ የሚፈጸምን ወሲባዊ ጥቃት መታገዝ እንደማይገባና ይቅር እንዳይባል ለማስገንዘብ ነው ብለዋል። ደቡብ ሱዳን እ.ኤ.አ ከ 2013 ጀምሮ በከባድ የእርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ

ስትሆን የሰብአዊ መብት ጥሰት በዜጎቿ ላይ በስፋት እንደምትፈጽምም የተለያዩ አለም አቀፍ ተቋማት ሪፖርት ያደርጋሉ።
********

የአሜሪካ ኢየሩሳሌም የእስራኤል ዋና ከተማነትን መቀበሏን ተከትሎ በአለም ዙሪያ ከፍተኛ ተቃውሞ አስነሳ

የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ኢየሩሳሌም የእስራኤል ዋና ከተማ ነች ብለው እውቅና መስጠታቸውን ተከትሎ በአካባቢውና በመላው አለም ጠንካራ ተቃውሞ እየተሰነዘረ ነው።የፍስጤየም ባለስልጣናት ህዝባቸው ሰፊ የተቃውሞ ሰል እንዲያደርግ በጠሩት መሰረት በዌስት ባንክ፣ ጋዛ ሰርጥና ምስራቅ ኢየሩሳሌም አደባባይ ላይ የተቃውሞ ሰልፎች ከሐሙስ እለት ጀምሮ እየተካሄደ ነው።በዚህምሁለት ሰዎች በእስራኤል ወታደሮች ሲገደሉ ከ 30 በላይ የሚሆኑ መቁሰላቸውን አልጀዚራ ዘግቧል።በቅርቡ የአሜሪካ ምክትል ፕሪዚዳንት ማይክል ፔንስ ከፍልስጤሙ መሪ መሐሙድ አባስ ጋር ሊያደርጉት ያሰቡትን የሰላም ድርድር አንዳንድ የፍልስጤም ባለስልጣናት ከማይክል ፔንስ ጋር የሚደረግ ውይይት እንደማይኖር እየገለጹ ነው።እየሩሳሌም በክርስትና፣ እስልምና እንዲሁም አይሁድ እምነቶች ትልቅ ሥፍራ የሚሰጣት ቦታ ስትሆን፤ እስራኤል በጦርነት አሸንፋ ከተማዋን የእኔ ናት ብትልም ዓለም አቀፍ እውቅና ሳታገኝ ቀርታለች።አሜሪካ እየሩሳሌም የእስራኤል ዋና ከተማ ናት ስትል ያወጀች የመጀመሪያዋ ሀገርም ሆናለች።በዚህም የአሜሪካ ወዳጅ ሀገራት ጭምር የዶናልድ ትራምፕ ውሳኔን ተቃውመዋል።